# የሼህ ሙሐመድ አል-አሙዲ ውለታ ተወርቶም ተጽፎም የሚበቃ አይደለም

**(ከፍቅሩ አየለ በላይ)**
fikruayelebelay@yahoo.com

ለዚህ ጽሑፍ መነሻ የሆነኝ በሰንደቅ ጋዜጣ 13ኛ ዓመት ቁጥር 635 እና 636 እትሞች ላይ ስለ ታላቁ ባለሀብት ስለ ሼህ ሙሐመድ ሁሴን አሊ አል-አሙዲ የወጡት ጽሁፎች ናቸው። እነዚያን ጽሁፎች ካነበብኩ በኋላ እኔም ስለዚያ ደግ ሰው የማውቀውን መጻፍ አለብኝ ብየ ይቺን መጣጥፍ ለሰንደቅ ጋዜጣ ላኩ። የተጣመመውን አቃንታችሁ፣ የተሳሳተውን አርማችሁ ታነቡልኝ ዘንድ አደራ እላለሁ።

ጽሁፌን የምጀምረው የእነ ሼህ ሙሐመድ ሁሴን አሊ አል-አሙዲንን የእስር ሁኔታ በተመለከተ ከመገናኛ ብዙሃን (በተለይም ከማህበራዊ ሜዲያ) ያገኘኋቸውን መረጃዎች በማካፈል እንዲሆን ወደድሁ።

ጊዜው እንዴት ይበራል ጃል!? የሳዑዲ መንግስት በሀገሩ ባለሀብቶችና በመንግስት ባለስልጣናት ላይ የፀረ-ሙስና ዘመቻ ከጀመረ ሦስት ሳምንታት ተቆጠሩ። ታሳሪዎቹ ያሉበትን ሁኔታ በተመለከተ እንደ አልጀዚራ ያሉ ታዋቂ ዓለም አቀፍ የዜና አውታሮች ጭምር የተለያዩ ዘገባዎችን እያቀረቡ ነው።

በማህበራዊ ሜዲያ (በፌስቡክ) ላይ "እነ ሼህ ሙሐመድ አል-አሙዲ በሳዑዲ ዓረቢያ መንግስት ባለስልጣናት እየተገረፉ ነው..." የሚል ነገር አነበብኩና በልቤ "ሰዎቹ የታሰሩት ኢትዮጵያ ውስጥ መስሏቸው ይሆን እንዴ ይህንን የጻፉት?" አልኩና አለፍኩት። ሌላ ቦታ ላይ ደግሞ "እነ ሼህ ሙሐመድ ፍራሽ ታድሏቸው የሚያድሩት ወለል ላይ ነው..." የሚል ነገር አገኘሁ። አሁንም በልቤ "... ሰዎቹ ቂሊንጦ ነው እንዴ ያሉት?" አልኩና ይህንንም በሳቅ በፈገግታ አለፍኩት።

ፕሬዝዳንት ትራምፕ በትዊተር ገጻቸው ላይ "አንዳንዶቹ... ሀገራቸውን ለዓመታት ሲያልቡ የነበሩ ናቸው..." በማለት በታሳሪዎቹ ላይ ተሳልቀዋል። የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት ቃል አቀባይ በበኩላቸው "የሳዑዲ መንግስት ... ባሰራቸው ሰዎች ላይ ክስ እንዲመሰርት እናበረታታለን" ማለታቸውም ተዘግቧል።

እነዚህንና መሰል ሁኔታዎችን ከማህበራዊ ሜዲያ ካነበብኩ በኋላ የአልጀዚራ ቴሌቪዥንን የእንግሊዝኛ ፕሮግራም ስከታተል በማህበራዊ ሜዲያ ላይ የተጠቀሱት ሃሳቦች ጋር ተመሳሳይ የሆነና በምስል የተደገፈ ዘገባ መቅረቡን አየሁ።

ቪኦኤ ያነጋገራቸው አንድ ምሁር በበኩላቸው "ሰዎቹ የታሰሩት በሙስና ብቻ ነው ብሎ መውሰድ አይቻልም። የተደበላለቁ ምክንያቶች አሉ። ... ከታሰሩት ውስጥ አንዱ ግማሽ ትሪሊዮን ዶላር ሃብት የሚያንቀሳቅሱ ባለሃብት ናቸው። ... አሜሪካ ውስጥ አንድ ቀን ጧት ቢልጌትስ እና ዋረን ባፌት መታሰራቸውን በዜና ብትሰሙ በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ የሚኖረው ጫናና አመኔታ ምን ሊሆን እንደሚችል እስቲ አስቡት ..." ነበር ያሉት።

ከላይ የጠቀስኳቸው ዘገባዎች የእነ ሼህ ሙሐመድ የእስር ሁኔታ አሳሳቢ መሆኑን የሚያመላክቱ ሆነው ነው ያገኘኋቸው። "በድብቅ የተቀረጹ ናቸው" ተብለው የተለቀቁ ቪዲዮዎች ላይ መደዳውን

የተደረደሩ ፍራሾች ይታያሉ። ፍራሹ ላይ የተኙት እነማን እንደሆኑ ግን ለይቶ ማወቅ አይቻልም። እነ ሼህ ሙሐመድ የታሰሩበት ሆቴል ራሱ መሆኑንም ማረጋገጥ አይቻልም።

አምስት ኮከብ ባለው ሆቴል ውስጥ ክብር ያላቸውና በሀገሪቱ አንቱ የተባሉ ቱጃሮችን ፍራሽ ላይ መደርደር አስገራሚ ትእይንት ነው - በፍራሽ መቀመጥ የዐረቦች ባህል ነው ካልተባለ በስተቀር! የኢንተርኔት ወሬ አያልቅም። ለመንደርደሪያ ይሆን ዘንድ ይህን ካልን ወደ አገር ቤት እንመለስ።

አንድ ሀዋሳ አካባቢ የሚኖር ጓደኛየ ከነገረኝ ልጀምር። “የወደቀን ግንድ ምሳር ይበዛበታል” እንዲሉ የሼህ ሙሀመድ መታሰር በመገናኛ ብዙሃን መዘገብ እንደተጀመረ ሐዋሳ ከተማ አቅራቢያ በሚገኘው የኤልፎራ ንብረት በሆነው በ“ሻሎ እርሻ” ላይ የተዘራውን አዝመራ የመዝረፍ ሙከራ ተደርጓል አሉ። መቼም አሉ ነው። የዘረፋው ምክንያት ምንድነው? ሲባል ደግሞ “የእርሻው ባለቤት በውጪ ሀገር ታስሯል፣ ከእንግዲህ መምጣት አይችልም፣…” የሚል ነው አሉ። አሁንም አሉ ነው።

ለዘረፋ የተሰማሩት ሰዎች መጠነ ሰፊ ጥፋት ሊያደርሱ የሚችሉ ቢሆኑም በአካባቢው ያሉ የመንግስት አካላት፣ የመከላከያና የፀጥታ ኃይሎች ከኤልፎራ ሰራተኞች ጋር በመተባበር በወሰዱት ፈጣን እርምጃ ችግሩ ሳይስፋፋ በቁጥጥር ስር ውሎ ጥፋቱ ተገትቷል መባሉንም ሰምቻለሁ። አሁን ይሄ ምን ይባላል? መንግስት ባለበት ሀገር? ከዚህ በፊት ዳንጎቴ ሲሚንቶ ፋብሪካ ላይ የሆነውን ሰምተናል። ባለ ሀብቶች እኮ ገንዘባቸውን የሚያፈሱት መንግስትንና ህግን ተማምነው ነው። በሀገሪቱ ባሉ ኢንቨስትመንቶች ላይ እንዲህ ዓይነት ወረራ የሚካሄድ ከሆነ በዚች ሀገር ኢንቨስትመንት የሚባል ነገር አደጋ ላይ ወድቃል። በዚሁ ከቀጠልን ብዙ ቢሊየን ብር ወጥቶባቸው እየተሰሩ ያሉት የኢንዱስትሪ ፓርኮች የሽረሪት፣ የዝንብና የአይጥ መዋያ መሆናቸው አይቀሬ ነው።

እንደኔ እንደኔ የሼህ ሙሐመድ መታሰርም ሆነ በኢትዮጵያ ውስጥ አለመኖራቸው ካቋቋሟቸው ኩባንያዎች ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት የለውም። የሼህ ሙሐመድ ኩባንያዎች ህጋዊ ሰውነት አላቸው። መብትና ግዴታዎችም አሏቸው። የሚቋቋሙበትና የሚፈርሱበት የህግ አግባብም አለ። ሼህ ሙሐመድ ኖሩም አልኖሩ፣ ታሰሩም ተፈቱ የኩባንያዎቹ ህልውና ይቀጥላል።

ኩባንያዎቹ የተቋቋሙበት መዋዕለ ንዋይ የሼህ ሙሐመድ ነው። ኩባንያዎቹን በኃላፊነት የሚመራውና እቅድ ይዞ ለውጤት የሚያበቃው ደግሞ የኩባንያዎቹ ማኔጅመንትና መላው ሰራተኛ መሆኑ መታወቅ አለበት። በዚህ አቅጣጫ ስናየው ሼህ ሙሐመድ ሁሴን አሊ አል-አሙዲ ኢንቨስተር ሲሆኑ፤ ሠራተኛው የኩባንያዎቹ ባለቤት፣ መሪና አስተዳዳሪ ነው ማለት ይቻላል።

ሌላው ለማንሳት የምፈልገው ነጥብ “ሼህ ሙሐመድ አል-አሙዲ ድሃዎችን ዞር ብለው አያዩም?” የሚለውን አሉባልታ ነው። በሼህ ሙሐመድ ላይ በተደጋጋሚ ከሚሰነዘሩ ትችቶች አንዱ “ሼህ ሙሐመድ በብዛት ድጋፍና እርዳታ የሚያደርጉት፣ ቢታመሙ የሚያሳክሙት የኪነ-ጥበብ ባለሙያዎችን ነው። ሌሎች ድሃዎችን ዞር ብለው አያዩም…” የሚል ነው። ይህ ትችት በብዙዎች ዘንድ ተደጋግሞ የሚደመጥ በመሆኑ የግል እይታየን ዘርዘር አድርጌ ለማቅረብ እሞክራለሁ።

ከሼህ ሙሐመድ የግል ባህሪ እንነሳ። ዩቲዩብ ላይ በተጫነ በአንድ ጥናታዊ ዘገባ ላይ እንዳየሁት ሼህ ሙሐመድ በልጅነታቸው ከፍ ያለ የኪነ-ጥበብ ፍቅር ነበራቸው አሉ። ወልዲያ እቴጌ ጣይቱ ብጡል ት/ቤት ይማሩ በነበረበት ወቅት ቅዳሜና እሁድ በት/ቤቱ አዳራሽ ከጓደኞቻቸው ጋር ሙዚቃና ቲያትር ያቀርቡ ነበር። ሼህ ሙሐመድ ጎበዝ ከበሮ መቺ ነበሩ አሉ። ነፍስያቸው በጥበብ ተለክፋለች። በዚያ ላይ ያደጉበት ማህበረሰብ (ወሎ) የኪነት አድባር የታነፀበት አገር ነው። በዚህም

ምክንያት ሼህ ሙሐመድ የኪነ-ጥበብ ሰዎችን ቢወዱና ቢያቀርቧቸው፣ በችገራቸውም ጊዜ ቢደርሱላቸው የሚገርም አይሆንም።

ሁለተኛ መታየት ያለበት ጉዳይ የኪነ-ጥበብ ሰዎች የህዝብ ሀብቶች መሆናቸው ነው። እነዚህ ከእጅ ወደ አፍ የሆነ ኑሮ የሚኖሩ የህዝብ ልጆች በተገኘው አጋጣሚ ድጋፍ ቢደረግላቸው ህዝብን እንደመደገፍ መቆጠር አለበት እንጂ ለግለሰቦቹ እንደተደረገ ልዩ ሁኔታ መወሰድ የለበትም የሚል እምነት አለኝ።

በሦስተኛ ደረጃ መታየት ያለበት ነጥብ ለአርቲስቶች የሚደረገው ድጋፍ ሰዎቹ ባላቸው ታዋቂነት ምክንያት ነገሩ ጎልቶ ህዝብ ጆሮ ስለሚደርስና እውቅና ስለሚያገኝ ነው እንጂ ለሌሎች ታዋቂ ላልሆኑ፣ የኪነ-ጥበብ ባለሙያ ላልሆኑ በርካታ ዜጎችም የተለያየ ድጋፍ አድርገዋል - ሼህ ሙሐመድ። ማሳያ ይሆን ዘንድ የተወሰኑ ምሳሌዎችን ልጥቀስ።

ለምሳሌ ሼራተን ሆቴል በተሰራበት አካባቢ ለነበሩ አምስት መቶ አባወራዎች በሲኤምሲ መንገድ በተለምዶ አልታድ ሚካኤል የሚባለው አካባቢ ቤት ሰርተው በነፃ ሰጥተዋል። እነዚያ ሰዎች አርቲስትም ከበርቴም አለመሆናቸውን ልብ በሉ! በወልዲያ ከተማ የዳሸን ባንክ ህንፃ በተሰራበት አካባቢ ለተነሱ የከተማዋ ነዋሪዎች “ሚድሮክ” የተሰኘ መንደር መስርተው፣ ቤት ሰርተው በነፃ ሰጥተዋል። እነዚያም ሰዎች አርቲስትም ከበርቴም አይደሉም።

ለልብ ህሙማን ማከሚያ የሚሆን ሆስፒታል የተሰራው እርሳቸው ወደ 33 ሚሊዮን ብር በመለገሳቸው መሆኑንም ዩቲዩብ ላይ ዶ/ር በላይ አበጋዝ እያለቀሱ ይናገራሉ። በቅርቡ እንኳ በቆሼ አደጋ ለደረሰባቸው፣ በሶማሌና በኦሮሚያ በተከሰተው ግጭት ለተፈናቀሉ፣… ወገኖች የተደረገውን እርዳታ መጥቀስ ይቻላል። እነዚህም ምንዱባን አርቲስትም ከበርቴም አይደሉም። በምግብ እጦት ምክንያት አዙሯቸው እየወደቁ መማር ለተቸገሩ በሺህ የሚቆጠሩ ተማሪዎች መመገቢያ የሚሆን በዓመት 26 ሚሊዮን ብር እየሰጡ መሆናቸውን የምናውቅ ስንቶች ነን? - ዩቲዩብ ላይ ቢፈልጉ ስለ ሼህ ሙሐመድ ብዙ ነገር ማወቅ ይችላሉ።

በአጠቃላይ ሼህ ሙሐመድ ድጋፍና እገዛ የሚያደርጉት ለአርቲስቶችና ለታዋቂ ሰዎች ነው የሚለውን አባባል ከላይ ከጠቀስኳቸው ነጥቦች አኳያ አቆራኝተን ብናየው መልካም ነው። በቁጥር ደረጃ ካየነው ድጋፍ የተደረገላቸው አርቲስቶች ብዛት በጣት የሚቆጠር ነው። የተለያየ ድጋፍ የተደረገላቸው ወገኖች ብዛት ግን የትየለሌ ነው።

ሀገራዊ አሻራ የታተመባቸውን ሌሎች የሼህ ሙሐመድ በጎ ተግባራትን እናንሳ። ሼህ ሙሐመድ ያከናወኗቸውን ሀገራዊ በጎ ተግባራት ዘርዝሮ ለመግለጽ አስቸጋሪ ቢሆንም ከሌሎች ባለሀብቶች ለየት የሚያደርጋቸውን አለፍ አለፍ ብየ ለመጥቀስ እሞክራለሁ።

በብዙዎች ዘንድ “የቁርጥ ቀን ልጅ” እየተባሉ የሚጠሩት ሼህ ሙሐመድ ሸራተን ሆቴልን የሰሩት በዚያ ወቅት በሀገሪቱ ከነበረው የቱሪዝምና የንግድ እንቅስቃሴ አኳያ ትርፍ ለማግኘት በማሰብ አልነበረም። ይልቁንም በወቅቱ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ካዛንቺስ አካባቢ ግዙፍ ዓለም አቀፍ የስብሰባ ማዕከል እያሰራ ስለነበር ለዚያ ህንፃ ምረቃ የሚመጡ የሀገር መሪዎች የሚያርፉበት ደረጃውን የጠበቀ ሆቴል እንደሚያስፈልግ በማሰብ ነበር ሼራተን ሆቴል የተገነባው። (በእንግዳ ተቀባይነቷ በምትታወቀው ሀገራችን የሀገር መሪዎች ማረፊያ አጥተው ወደ ጎረቤት ሀገር ሄዱ እንዳይባል፤ የሀገር ገጽታ እንዳይበላሽ ማለት ነው)

የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት በተቀሰቀሰበት ወቅት ሼህ ሙሐመድ ያደረጉት በጎ ሀገራዊ ተግባርም እዚህ ላይ መነሳት የሚገባው ነው። በዚያ ወቅት በሀገራችን ላይ ማዕቀብ ተጥሎ ነበር። በእንቅርት ላይ ጆሮ ደገፍ እንዲሉ ጦርነትና ማእቀቡ አላንስ ብሎ በሀገሪቱ ድርቅና ርሃብም ተከስቶ ነበር። መንግስት እንኳን የድርቅ አደጋውን ሊመክት የወታደሮቹን ትጥቅና ስንቅ ለማሟላት የተቸገረበት ወቅት ነበር። ይህንን የተገነዘቡት ሼህ ሙሐመድ እህል ወደ ኢትዮጵያ እንዲገባ በማድረግ ወገናቸውን ታድገዋል።

የዛሬ ሰባት ዓመት ገደማ ሀገሪቱ የዶላር እጥረት አጋጥሟት ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዋ አጣብቂኝ ውስጥ ገብቶ ነበር። ይህንን የሰሙት ሼህ ሙሐመድ ውጪ ሀገር ካላቸው ሀብት ላይ አንድ መቶ ሺህ ዶላር አስመጥተው ዳሽን ባንክ እንዲቀመጥ በማድረግ ወቅታዊ ችግሩ እንዲፈታ ጥረት ማድረጋቸው በወቅቱ በሰፊው ይወራ ነበር።

በጋዜጠኛ ተጠይቀው "ለዚህ ግድብ የለበስነውን ልብስ እንኳ ብንሸጥ የሚያንሰው ነው" ያሉት ሼህ ሙሐመድ ለህዳሴው ግድብ ግንባታ በአንድ ጊዜ ያዋጡት አንድ ነጥብ አምስት ቢሊዮን ዶላር ለሌሎች ባለ ሀብቶችና ዜጎች ትልቅ የሞራል ብርታትና መነሳሳት መፍጠሩ በዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙሃን ጭምር ተደጋግሞ የሚወሳ ተግባር ነው።

በአንድ ወቅት "የአፍሪካ ህብረት ዋና ከተማ የት ይሁን" የሚለው ክርክር ተነስቶ የሊቢያው ፕሬዝዳንት ጋዳፊ ወደ ትሪፖሊ እንዲዛወር ቅስቀሳ ባደረጉበት ወቅት ኢትዮጵያ አታሟላም ብለው ያቀርቡት የነበረው ጉድለት ለመሪዎች የሚሆን ምቹ የትራንስፖርት አቅርቦት ነበር። ይህንን የሰሙት ሼህ ሙሐመድ በሁለት ሳምንት ውስጥ 60 ዘመናዊ መርሰዲስ አውቶሞቢሎችን በአውሮፕላን አጓጉዘው በማምጣት ለመንግስት በእርዳታ መልክ መስጠታቸውና ያንን ክፍተት መሙላታቸው የጊዜ መርዘም የሚያስረሳን አይሆንም።

በኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር ሁለተኛው ሚሊኒየም ሊከበር ዝግጅት እየተደረገ ባለበት ወቅት ለበዓሉ ማክበሪያና ለስብሰባ የሚሆን ሃያ ሺህ ሰው የሚይዝ አዳራሽ አስፈለገ። መንግስት ይህንን ለማድረግ የሚያስችል እቅድም በጀትም አልነበረውም። ይህንን የሰሙት ሼህ ሙሐመድ "አለሁ" ብለው ተነሱና ብረትና ምስማር ጭምር በአውሮፕላን እያስመጡ በስድስት ወራት ውስጥ የሚሊኒየም አዳራሽን አስገንብተው ለበዓሉ እንዲደርስ አደረጉ።

ሼህ ሙሐመድ ያከናወኗቸው ሀገራዊ አሻራ የታተመባቸው ተግባራት በርካታ ናቸው። ለማስታወስ ያህል እነዚህ ከላይ የጠቀስኳቸው ይበቃሉ። እነዚህ ሁሉ በጎ ተግባራት ለሚወዷት ሀገራቸው ያደረጉት እንጂ ተጨማሪ ሀብት የሚፈጥርላቸው እንቨስትመንት አልነበረም። "የችግሮች መፍቻ ታግሎ መስራት፣ ተስፋ አለመቁረጥ፣... ነው" የሚሉት ሼህ ሙሐመድ "ለምንድነው በሀገርዎ ላይ መዋዕለ-ንዋይ ማፍሰስ የሚወዱት?" ተብለው ሲጠየቁ የሚሰጡት መልስ የሚያስገርም ነው።

በኢትዮጵያ ከአራት እስከ አምስት ቢሊየን ዶላር የሚሆን ኢንቨስትመንት እንዳላቸው ከዓመታት በፊት ለኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የተናገሩት ሼህ ሙሐመድ "ምኞቴ በሀገሬ በየወሩ አንድ አንድ ፋብሪካ መክፈት ነበር... የሀገሬ ወጣቶች ሀገራቸውንና ራሳቸውን ጠቅመው በዓለም ታዋቂ እንዲሆኑ ነው ፍላጎቴ። በሀገር ቤት ያሉ ኩባንያዎቼ ከሚያፈሩት ሀብት 5 ሣንቲም ወስጄ አላውቅም። እዚያው በዚያው ኢንቨስትመንት እንዲያስፋፋና ብዙ ወጣቶች የሥራ እድል እንዲያገኙ ነው ምኞቴ" ይላሉ ሼህ ሙሐመድ። በአጭር አነጋገር - ሼህ ሙሐመድ በኢትዮጵያ ኢንቨስት የሚያደርጉት ወገናቸውን ከድህነት ለማላቀቅ ነው። አራት ነጥብ!!!

የሼህ ሙሐመድ ቀኝ እጅ እንደሆኑ የሚታወቁት ዶክተር አረጋ ይርዳው “የፒራሚዱ ጫፍ” በሚል ርእስ ለታተመ መጽሐፍ የሰጡት አስተያየትም ከላይ የተጠቀሰውን የሼህ ሙሐመድን አባባል የሚያጠናክር ነው። “የሼህ ሙሐመድ ኢንቨስትመንት በትርፍ ላይ የተመሰረተ ኢንቨስትመንት አይደለም። ዓላማቸው ወገንን መርዳት ነው። ደካማ ሰራተኛ ቢሆን እንኳ ሊሰራው ወደሚችለው ስራ እንዲዛወር ይደረጋል እንጂ አይባረርም። ‘ተውት። ገለል አድርጉት እንጂ ደመወዙን አትከልክሉት’ ነው የሚለው ሙሐመድ…” ይላሉ ዶ/ር አረጋ።

ይህ ኢትዮጵያን ወዳድ፣ ይህ ወገኑን አፍቃሪ፣ ይህ የክፉ ቀን ደራሽ፣ ይህ ደግ ሰው በሌብነት የሚኮነን ሰብእና የላቸውም። በስራ የሚተጋ እንጂ በሙስና የሚያስጠረጥር ሰብእና የላቸውም። በአስቸኳይ እንዲፈቱ በፆም በጸሎት አንለያቸው !